# ዓባይ እንደዋዛ፤ ግድቡን ከጥላቻ አንጻር ማየት አደገኛ ነው

# ክፍል አራት

አክሎግ ቢራራ ዶ/ር

የዚህ ተከታታይ ፅሁፍ መሰረታዊ ሃሳብና ትንተና፤ **ኢትዮጵያ ዓባይንና ሌሎች ወንዞቿን** የራሷን ኢኪኖሚ ዘመናዊነት፤ ለሕዝቧ የምግብ ዋስትና ስኬታማነት፤ እያደገ ለሄደው ወጣት ትውልድ የስራ እድል የመፍጠር ወዘተ መብት ያላት መሆኑን የሚያጠናክር ነው። The **Nile is African and Ethiopia is its hub** በሚል አርእስት ለአለጀዚራ ያቀረብኩት ፅሁፍ ይኼን ይገባኛልነት በማስረጃ ተደግፎ ያሳያል። በአረብኛ የተተረጎመው ትንተና የብዙ አንባቢዎችን አስተሳሰብ እንደቀሰቀሰ ሰምቻለሁ፤ አሉታዊና ነቀፋ ያለበት ትችት አልደረሰኝም። የኢትዮጵያን ይገባኛልነት ሌሎች የጥቁር አፍሪካ ተፋሰስ አገሮች እንደሚደግፉም አሳይቻለሁ።

አከራካሪ ሆኖ ያየሁትና በተከታታይ ለመተንተን የሞከርኩት የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና ይገባኛልነት ከጥያቄ ውስጥ ለማስገባት አይደለም፤ ለማጠናከር ነው። ገዢውን ፓርቲ መቃወምና የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም መደገፍ የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን አሳይቻለሁ። የኢትዮጵያ ይገባኛልነት፤ ዘላቂ ጥቅምና ደህንነት ከጥያቄ ውስጥ መግባትና ለፖለቲካ መንደርደሪያና መጠቀሚያ ሊሆን አይገባውም እላለሁ። ኢትዮጵያ የባህር በሯን አጥታ ዓባይንም ማጣት ለተከታታይ ትውልድ በደል ነው። ለማስታወስ አፄ ኃይለሥላሴና ደርግ ለማልማት የሞከሩትን ዓባይ ዛሬ እድል ተገኝቶ የተሃድሶ ግድብ ስራ መጀመሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ሂደት የተገኘ ነው። ሕዝቡ በመንፈሱም፤ በጉልበቱም፤ በገንዘቡም እንደሚደግፈው እንሰማለን። ለኢንቬስትመንቱ የሚፈሰው ኃብት የህወሓት/ኢህአዴግ የግል ኃብት አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ኃብት ነው። ጥቅሙም ለኢትዮጵያ ሕዝብ መሆን አለበት።

የዚህ ትንተና መሰረት እንደ ተሃድሶ ግድብ ያለ **የኢኮኖሚና የሃግር ጥንክርና ለማስገኘት የሚያስችል ፕሮጀክት ከፖለቲካው ፍትሃዊነትና ከሃብት ስርጭት ሚዛናዊነት** ተለይቶ ሊታይ አይችልም የሚል ነው። ይክ ከሆነ የግድቡ ጥቅም ለገዢው ቡድን ብቻ መዋሉ አይቀርም። የህወሓት መስራቾችና መሪዎች ለጥቂቶች ጥቅም **“ስልጣን ወይም ሞት”** ብለው በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ የጫኑት አደገኛ የከፋፍለህ ግዛው የአገዛዝ ስርዓት ዛሬ ወደ ከፍተኛ አደጋ እያመራ ነው። የተሃድሶ ግድብ ቢሰራም ባይሰራም አሁን ያለውን ቀውስ ሊፈታውና ሊገታው አይችልም። ከጅምሩ ስርዓቱ በማይታረቁ የብሄር፤ ብሄረሰብና ሕዝቦች ልዩነቶች፤ የተፈጥሮ ኃብትን ለተወሰነ ቡድን ባለቤትነት በማሸጋገር፤ ይኼን ስኬታማ ለማድረግ መብቶችን በማፈን ወዘተ ላይ የተመሰረተ ነው። ሕዝብ ከሕዝብ እየለያዩ፤ መሬትን ቆራርሶ ለጥቂቶች ጥቅም እያስተላለፉ፤ ህወሓት በዋና ጠላትነት የፈረጃቸውን ከመሬትና ከሃብታቸው እያስለቀቀና እያደኼየ፤ ሰላምና እርጋታ ለመፍጠር አይቻልም። የስርዓቱ አገልጋይነት ለጭቁኖች መብትና የኑሮ መሻሻል አለመሆኑ በይፋ ሲከሰት ቆይቷል። የኦሞ ሸለቆን፤ የጋምቤላን፤ የቤኒ ሻንጉል ጉሙዝን፤ የአፋርን፤ የኦጋዴንን “ጭቁን” ሕዝብ ከጢቂቶቹ አዲስ ባለኃብቶች ጋር ብናነጻጽር ህወሓትና ደጋፊዎቹ ለማን ጥቅም እንደቆሙ ለማየት አንቸገርም። የጥቂቶች ስልጣን ሊቆይ የቻለውና የሚቆየው የእርስ በርስ ጥላቻንና ግጭትን በማቀጣጠል፤ ሰብአዊ መብቶችን ፍፁም በሆነ መንገድ በማፈን፤ በተለይ የአማራውንና የኦሮሞውን ሕዝብ በማጋጨት፤ እልቂት እንዲስፋፋ በማድረግ፤ አብሮ በመስራትና አብሮ ችግሮቾን በመፍታት ፋንታ ህብረተሰቡን በማራራቅ፤ ባጭሩ በውይይትና በዘዴ ሰላምና እርቅ ስኬታማ እንዳይሆን በማድረግ ነው። ታዛቢዎች አስቸጋሪ ሆኖ ያገኙት አንዳንድ ለፍትህና ለዲሞክራሲ የቆሙ ስብስቦች የህወሓትን የጥላቻ ፈለግ ተከትለው ከሳቱ ላይ ቤንዚን መጨመራቸው ነው። ዙሮ ዙሮ የጥላቻ ፖለቲካ የሚረዳው የሚቃወሙትን ህወሓትን መሆኑን ዋጋ አልሰጡትም። ጥላቻን በጥላቻ፤ እልቂትን በእልቂት፤ አፈናን በአፈና፤ የቂም በቀልን በቂም በቀል ወዘተ የሚተካ ወይንም እነዚህን የመሰሉ የፖለቲካ ባህሎችና ልምዶች የሚያጠናክር ስብሰብ ወይንም ግለሰብ “ለቆመለት ሕዝብ” እውነተኛ አገልጋይ መሆኑ ያጠራጥራል። ህወሓት የሚፈልገውን የሚያደርግ መሆኑ ግን አያከራክርም። ለፍትህና ለእውነተኛ እኩልነት መቆምና የብሄር፤ ብሄረሰብ፤ ኃይማኖት ጥላቻን ማራገብ ሰማይና መሬት ናቸው። አይገናኙም።

የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ የስራ እድል፤ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት ሚዛናዊና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ካልተሰተካከለ ግጭት መነሳቱ አይቀርም፤ እየተሰፋፋ መሄዱን እያየን ነው። የጎሳ ጥላቻ ፖለቲካ የሚወልደው ጥላቻንና የከረረ መከፋፈልን እንደሆነ ቀደም ብለው ያሳሰቡ ብዙ ሁሉንም ብሄር፤ ብሄረሰብ፤ ፆታ፤ እድሜና ኃይማኖቶች የሚወክሉ ኢትዮጵያውያንና ፈረንጆች ነበሩ፤ አሁንም አሉ። የሚያዳምጥ አልተገኘም። እንዲያውም፤ ሌሎቻችን ፍልስፍናውን ተቀብለን የዚህ የጥላቻ ፖለቲካ ሰለባ ሆነን ሁሉን ነገር የምናየው በጥላቻ መነፅር ሆኗል። **ዛሬ፤ ሰብሳቢና ሁሉን አስተናጋጅ የሆነ የፖለቲካና የማህበረሰብ ማእከል የለም።** በክፍል ሶስት **“ኢትዮጵያ ሃገሬ፤ ዜግነቴ ኢትዮጵያዊ ነው”** በሚል አርእስት የዓባይን ኢትዮጵያዊነት ያቀረብኩበት ዋና ምክንያት ይኼን አደገኛ ክፍተት በማጤን ነው። ማእከል ይኑረን የሚል። ረጂም ታሪክ ያላት ቻይና ብሄራዊ አንደነቷ የተመሰረተው ህልምና ለሃገሩ ራእይ በነበረው አፄ ኪን ሺ ኋንግ በ221 B.C. ነበር። እኛም ተመሳሳይ ታሪክ አለን ስንል የለም ተብለናል፤ እድሜ ለህወሓት መስራቾችና ደጋፊዎች። ታሪኳን የተቀበለችውና የምታከብረው ቻይና ዛሬ ብሄራዊ (አገር አቀፍ) ኢኮኖሚ መስርታ፤ እድገቷና ልማቷ ብሄር፤ ብሄረሰብ፤ ኃይማኖት ወዘተ አይለይም። ከኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ጋር ሲነጻጸር፤ የቻይና ወጣት ትውልድ በአገሩ የወደፊት ዘላቂና ፍትሃዊ ልማት ያምናል። ቻይና ፈጣን የኢኮኖሚና የማህበራዊ ለውጥ የጀመረችው ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ሁለት ዓመታት በፊት ነው። ብሄራዊ ህልም፤ ራእይና አገር ወዳድነት፤ ማለትም፤ ቻይናዎች “ቻይና ሃገሬ፤ ዜግነቴ ቻይናዊ ነው” ብለው ቆርጠው ስለተነሱ፤ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የአሜሪካን ኢኮኖሚ ውጤት እንደሚበልጡ ይወራል። የአብዛኛው የቻይና ሕዝብ ኑሮ በጣም ተሻሽሏል፤ ወደፊትም

እየተሻሻለ እንደሚሄድ ይነገራል። በቻይና እድገት ጠቅላላ ገቢን ማሳደግ ብቻ እይደለም። ለጥቂቶች አገልጋይ የሆነ እድገት ማሳየት ብቻ አይደለም። አገር ወዳድ በመሆናቸው ቻይናዎች የራሳቸውን እድገትና ልማት ከሃገራቸው ልማት፤ ሃብታምነትና ታላቅነት ለይተው አያዩም። ባለፈው ዓመት የፒው የህዝብ ዘገባ ስድሳ ሶስት በመቶ የሚሆነው የቻይና ሕዝብ ኑሮው እየተሻሻለ እንደሚሄድ አስታውቋል። በአገሩና በአመራሩ እምነት አለው ማለት ነው። አብሮና ተደጋግፎ ማደግን ያቀፈ ስርዓት ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ይኖረዋል ማለት ነው። ብዙ የቻይና ልሂቃን እድገታዊ መንግሥት አገር ወዳድና ሁሉን አስተናጋጅ ሲሆን፤ በአንድ ፓርቲም ቢገዛ የተሻለ የማምረት፤ የአገልግሎት፤ የመንፈሳዊ ጥንክርና ወዘተ ብቃት ይኖረዋል የሚሉት ከላይ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች በመመርኮዝ ነው። ቻይና ብዙ ያልተፈቱ ግዙፍ--የፖለቲካ፤ የአካባቢ አጠባበቅ፤ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ጥያቄ፤ የባህር ይገባኛልነት ወዘተ- ችግሮች እንዳሉባት ይነገራል። ዘገባው የሚያሳየው አስደናቂ ክስተት ግን እነዚህ ሁሉ እንደሚፈቱ ነው። አገር ወዳድ አመራር ዙሮ ዙሮ እምነትና ጥንካሬ ይወልዳል ማለት ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ (**The Silent Majority**) አገሩን ይወዳል። በኢትዮጵያዊነቱ ያምናል። ባያምን ኑሮ ህወሓት በሚቀሰቅሰው ግፊትና ሴራ ሰፊ እልቂት ይፈጸም ነበር። ስለሆነም፤ አክራሪዎች እንደሚሉት ሳይሆን፤ ይህ ብልህ ሕዝብ አብሮ በሰላም ለመኖር፤ አብሮ መብቱን ለማስከበር፤ አብሮ ድህነትን ለማጥፋትና አብሮ ለመስራት ወዘተ የሚመኝ ሕዝብ ነው ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም። በማእከል ሆኖ እንዲግባባና አቅሙን እንዲያጠነክር የሚመራው የለም። ማእከል ይኑረን ስል ለአብዛኙው ሕዝብ መብት እንቁም፤ መብቱ እንዲከበር በአንድ ላይ፤ ለአንድ ብሄርዊ ዓላማ እንሰብሰብ፤ ለወደፊቱ ትውልድ ሰብሳቢ ህልምና ራእይ ይኑረን ማለቴ ነው። የንጉሳዊ ወይንም የደርጋዊ ስርዓት ተመልሶ ይተካ ማለቴ አይደለም። የዱሮውን እንመልስ (Restoration) ብለው የሚከራከሩ ልሂቃን ወይንም የፖለቲካ ስብስቦችና ፕሮግራሞች አላየሁም። ይህ ወደኋላ እንመለስ የሚል አስተሳሰብ ሰው ሰራሽ፤ ጠብ ጫሪ ነው። በኔ ግምት ወደኋላ መመለስ አይቻልም። የጉልተኛ ስርዓት አልፏል። ጉልተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ፈልጌ አላገኘሁም። አስፈላጊም አይደለም። ደርግና የግራው ክንፍ ለኢትዮጱያ ሕዝብ ካበረከታቸው አስኳል ፖሊሲዎች "መሬትን ላራሹ" ማድረጉ ነው። ልክ እንደ ቻይና ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ችሎታ ያላቸው፤ ባልተዛባ እድል የሚያምኑ፤ አገራቸውን የሚወዱና የሕዝብ አገልጋይ የሆኑ እንዲመሩ እናደርግ። ልክ እንደ ብራዚልና ችሌ፤ በሕዝብ የተመረጡና ለሕዝብ አገልጋይ የሆኑ ግለሰቦች አገሪቱን እንዲመሩ ሁኔታዎችን እናመቻች። ይኼ ሁለተኛው ተፈላጊ አማራጭ ያለነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ስኬታማ ሊሆን አይችልም። የሚያሳዝነው ጊዜና እድል እያመለጠን ነው። ወይ ቻይናን አልሆን፤ ወይ ችሌን አልሆን። ወይ ሶሻሊስት አልሆን። ወይ የገበያ ካፒታሊስት አልሆን። ባጭሩ ለማለት የሚቻለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመኘው ወደኋላ መመለስ ሳይሆን ሁሉን አሳታፊ የሆነ፤ በሕግ የበላይነት የሚዳኝ ዲሞክራሳዊ ስርዓት ነው። ምን አይነት ዲሞክራሲ የሚለውን የሚወስነው ሕዝቡ እንጅ የስልጣንና ጥቅምና በተራቸው ኪራይ ፈላጊዎች ሊሆኑ አይችሉም። ቅደመ ሁኒታዎችን ደርድር ማነቆ ማድረግ ለለውጥ አለመዘጋጀትን ያሳያል።

የህወሓት መሪዎች የሕዝብ ስብጥርነት (ethnic and religious diversity) ከሕግ የበላይነትና ከዲሞክራሳዊ ስርዓት ጋር አብረው አይሂዱም እያሉ ሕብረተሰቡን ለአደጋ ጋብዘውታል። ንኡስ ቡድን ሁል ጊዜ የሚከተለው ስልት ይኼው ነው። ፍልስፍናው የጥቂቶችን የበላይነት ለማጠናከር ነው። ሕንድ የልዩ ልዩ ብሄር፤ ብሄረሰብና ኃይማኖቶች አገር ናት። ጥንካሬዋ በሕዝብ ድምፅ፤ በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ መገዛቷ ነው። የግለሰብ ሰብእነትንና መብትን፤ ህንዳዊነትን፤ በሕግ ፊት እኩልነትን ወዘተ የተቀበለች አገር ናት። እኛም እነዚህን መስፈርቶች የመቀበልና ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለብን። ሕንዶች "ሃገሬ ሕንድ፤ ዜግነቴ ህንዳዊ ነው" ለማለት የቻሉት ልዩነቶችን ተቀብለው ማህበራዊ ችግሮችን በአንድነት ለመፍታት ስለወሰኑ ነው። ቻይና በልማታዊ መንግሥት ትመራለች፤ ሕንድ በዲሞክራሳዊ መንግሥት ትመራለች። ሁለቱም የሚመኙት ከድህነት የተላቀቀና በራሱ የሚመካ ታላቅነትን ነው። አድልዎና ሙስና የጠነከረባት ሕንድ ሲክ፤ ሂንዱ፤ የስልምና ኃይማኖት ወይንም ሌላ መለያ ሳይገታት በተከታታይ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫን ተጠቅማለች። አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ሞዲ ሙስናን ለማጥፋትና አገሪትን በፍጥነት ለማሳደግ ቃል ገብቶ ሲመረጥ ድጋፍ ያገኘው ከሁሉም ህንዶች ነው። ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ለሕንድ ሕዝብ አማራጮችን ለግሶታል። ኢቶጵያውያን ተመሳሳይ እድል ይፈልጋሉ። አብዛኛው የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ በጎንደር፤ በደሴ፤ በባህር ዳር፤ በአዲስ አበባ፤ በግምቢ፤ በሃረር፤ በአዋሳ ወዘተ ሰላማዊ ሰልፍ የሚያደርገው የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ቆርጦ በመነሳት ነው። ባጭሩ፤ የህወሓት ዓመራር ቢወድም ባይወድም፤ ቢፈቅድም ባይፈቅድም፤ አዲሱ ትውልድ "መብቴ ይከበር" ብሎ አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ ከተነሳ 94 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን በመሳሪያ ኃይል ሊገዛ አይችልም። በገፍ ሊጨፈጭፍ አይችልም። በቅርቡ በስዊድን አገር አንድ የትግራይ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ያሉት አግባብ አለው። **"<u>በጎሳና በክልል ተለይቶ የሚንጎበጎበው የጥላቻ ፖለቲካ</u>** መጠኑ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ አስግቶኛል። እርቅ ብቻ መፍትሄ ነው።" በአሁኑ ወቅት፤ የህወሓት በጎሰኛነት ላይ የተመሰረተ ጥላቻን ፈጣሪ አገዛዛ የራሱን ህልውና ጭምር ለአደጋ እየዳረገው ነው የሚሉ ብዙ ናቸው። በኢህአዴግ ውስጥም ስጋትና ፍርሃት እንዳለ በሚካሄደው ታይቶ የማይታወቅ አፈና፤ እስራትና ግድያ ለማየት ቀላል ነው። አፈናው ብሄር፤ ብሄረሰብ፤ እድሜ፤ ጾታና ኃይማኖት አይለይም። በተመሳሳይ፤ የወጣቱ ትውልድ መብቴ ይከበር ዘመቻ በምንም የሚቆም አይመስለኝም። ፍትህ፤ ዲሞክራሲ፤ እርጋታና ሰላም ከሌለ የተሃድሶ ግድብ ለአደጋ ይጋለጣል። በተጨማሪ፤ ማጤን ያለብን ሌላ አበይት ጉዳይ አለ። ይኼውም ሁኔታዎች እየተበላሹ ከሄዱ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ሊካሄድ ይችላል፤ ልክ ታይላንድ እንደሆነው። ልክ በግብፅ እንደተከሰተው።

**የማይለያየውን የኢትዮጵያን ሕዝብ አንለያየው**

ኢትዮጵያ የዓባይን ወንዝ የመጠቀም፤ የተሃድሶን ግድብ ለሕዝቧ ጥቅም የመገደብ፤ ከተሃድሶ ባሻገር ዓባይንና ሌሎቹን ወንዞቿን ለመሰኖ እርሻ የመጠቀም ሙሉ መብት አላት። ሆኖም፤ የተሃድሶን ግድብ ከመገደብ ባሻገር መታየት ያለባቸው አስኳል ጉዳዮች አሉ። ዋንውና ተቀዳሚው የኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነት፤ መብትና የዲሞክራሳዊ አገዝዝ ስኬታማነት ነው እላለሁ። በምሳሌ ልጀምርና ወንድማማች፤ እትማማች የሆነውን የኤርትራንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ለያይቶ ከሱዳንና ከሌሎች ሕዝቦች ጋር የኢኮኖሚ ጥቅም

ግንኙነት መፍጠር ጠቃሚነቱ ወቅታዊ እንጅ ዘላቂ አይደለም፡፡ በመጀመሪያ መጠናከር ያለበት በጋብቻ፤ በኃይማኖት፤ በባህል፤ በታሪክ፤ በኩታ ገጠምትነት፤ በወደፊት እድል፤ በባህር ተጠቃሚነት ወዘተ ያለውንና መኖር የሚገባውን ግንኙነት ማጠናከር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኤርትራ ሕዝብ ተለይቶ መኖር ለሁለቱም ሕብረተሰቦች፤ በተለይ ለወጣቱ ትውልድ በደል ነው። የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝብ ከአሁኑ አፋኝና ጎጅ የፖለቲካ አመራር ወጥቶ በመካከሉ ያለውን የማይካድና የማይፋቅ ግንኙነት ማጠናከር ለሁሉም ህብረተሰቦች ጥንካሬ፤ እድገትና ልማጥ ያገለግሳል። ለምሳሌ፤ የውሃ ኃይል አመንጭቶ ለኤርትራ የመብራት ፍላጎት ጥቅም እንዲውል መደራደር ብልሃት ነው። የባህር በር ለመብራት ኃይል የሚል ድርድር ማለቴ ነው። በተመሳሳይ፤ ብዙ የኦሮሞ ተወላጅ ምሁራንና ሌሎች እንደሚሉትና እኔም ከዱሮ ጀምሮ እንደማምነው የኦሮሞ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለኢትዮያ ብሄራዊ አንድነት፤ ዘላቂና ፍትሃዊ እድገት ቁልፍ መሆናቸውን መቀበል ግዴታችን ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ነጻነት ያደረገርው አስተዋፆ ቀላል አይደለም። ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና ነጻነት የታገለና የሞተ ሕዝብ ከራሱ ሊገነጠል አይችልም እላለሁ። በበኩሌ ይህ አንጋፋ ሕዝብ “መብቴ ይጠበቅ እንጂ ከራሴ ልገንጠል” የሚል አይመስለኝም። ሆኖም፤ መብቱን ገፎ ለመገንጠል አትችልም ማለት ሞኝነት ነው። ለማለት የምንገደደው ልክ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚመኘውና እንደሚፈልገው የሁሉም ኢትዮጵያውያን መብቶች ይከበሩ። ሁሉም ኢትዮጵያውያን በሃገራቸው ለመመከታ እንዲችሉ መብታቸው መከበር አለበት። ሌሎቻችን ለመርዳት የምንችለው ሁኒታዎችን በማባባስ አይመስለኝም። “ህወሓት ለያይተህ መጨፍጨፍክን አቁም” በሚል መርህ ይመሰለኛል። ዓላማው ማን ይግዛ፤ ማን ወደጎን ይተው ወዘተ አይመስለኝም። ችሎታና ብቃት ያለው፤ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን እኩልነት የሚያስብ፤ በሕግ የበላይነት የሚዳኝ ወዘተ እንዲመራ ሁኔታዎችን እናመቻች። ለዚህ ዘመናዊ የሆኑ የድርድር አማራጮች አሉ፤ ለምሳሌ ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ገዢው ፓርቲ የሚሳተፉበት ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ተካሂዶ ሕዝብ የሚወስነው ውጤት ይከበር የሚል። በተቃዋሚው ጎራ የዓላማ አንድነት ካለ መብቶች መከበራቸውና ዲሞክራሳዊ ስርዓት መፈጠሩ አይቀርም። ምክንያቱም፤ ህወሓት አብዛኛውን ኢትዮጵያ አይወክልም። ለመወከልም አይችልም። ይኼን ስኬታማ ለማድረግ፤ በአንድ ላይ፤ አገር አቀፍ በሆነ የሕዝብ እንቅስቃሴ መነሳት ይበጃል። ገዢው ፓርቲ ከሁሉም በላይ የሚፈራው አብሮና ተባብሮ አገርን የማዳን፤ ሕዝብን ከከፋ እልቂት የመታደግ ብሄራዊና ሕዝባዊ ትግል ነው።

**ግድብ የሚሰራ አቅምን ለማጎልመስ ነው**

በዓባይ አርእስት ላይ ብዙ የድጋፍና የተቃውሞ ትንተናዎች ይካሄዳሉ። ይሕ ጥሩ ነው። ማንም ግለሰብ ሃሳቡን የመግለፅ መብት አለው። አሉታዊ ሆነ አወንታዊ የሆነ ትንተና የሚያቀርቡት ትክክል አይደሉም ወይንም ናቸው ለማለት አንችልም። በማስረጃ እስካቀረቡ ድረስ ፈራጁ የኢትዮጵያ ሕዝብና የሚያገኘው ጥቅምና ታሪክ ብቻ ነው ብለን እንተወው። አስቸጋሪ ሆኖ ያገኘሁት ትንተናው የህወሓትን መንግሥት ዓመራር ጥላቻ መስፈርት ሲያደርግ የሚታየው አደጋ ነው። የፖለቲካ ባህላችን የማንፈልገውንና የምንቃወመውን መንግሥት መኮነንና ማጥላላት ነው። የህወሓት መስራቾች በዚህ የተካኑ ናቸው። ከማንኛውም ክፍል ይምጣ፤ የጥላቻን ፖለቲካ በጥላቻ ለመታደግ አይቻልም። ህወሓት የፈጠረብን ጥላቻ ይበቃል ብንል የተሻለ ውጤት እንቀዳጃንለን የሚል ግምት አለኝ። መንግሥት የሚተካ መሆኑን ካመንን፤ (እኔ ይተካል የሚል ግምት አለኝ) የኢትዮጵያን የባለቤትነትና ግድቡን የመስራት መብት በመንግሥት ጥላቻ አንጻር ማየቱ የአሁኑን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱንም ትውልድ ይጎዳዋል። የኢትዮጵያን ደህንነትና ዘላቂ ጥቅም በማይመለስ ደረጃ ይጎዳል። አግባብ ያለው ክርክር ግድቡ ከምን ጥቅምና ለማን ጥቅም ይውላል የሚለው ነው። አለበለዚያ መጻረሩ ለግብፆች መሳሪያ ይሆናል። ከጥላቻ በላይ ስናየው የተሃድሶ ግድብ ያለውን የኢኮኖሚ፤ የማህበረሰብ፤ የስራ እድል ማጣት፤ የምግብ ዋጋ ግሸበት፤ የምግብ እጥረት ወዘተ ችግር ይፈታል ለማለት አያስችልም። የበለጠ የሚጠቅመው የመስኖ ግድብ መሆኑ አያከራክርም። የግድቡን መብራት ለውጭ አገሮች ሽጦ ኢትዮጵያን ለማልማትና ለመመገብ አይቻልም። ተሃድሶ የምግብ ዋስትና አያስገኝም። ግድቡ ለመስኖ ስራ አያገለግልም። የመስኖ ግድቦች መስራት ግዴታ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለማስመር እፈልጋለሁ። ልክ ተሃድሶ እንደሚሰራው የመስኖ ግድቦችም በብዛት መሰራታቸው አይቀርም። ደርግ ሳሊኒ የተባለውን የጣሊያን ኩባንያ ተኮናትሮ ሰርቶት የበረው፤ ህወሓት ያፈራረሰው ጣና በለስ ጥሩ ሞዴል ነበር። ልምን ፈረሰ የሚለውን በሌላ ትንተና አሳያለሁ። ሌላው አከራካሪ ጉዳይ ኢትዮጵያ ዓባይን ለመገደብ  የኢኮኖሚ፤ ገንዘብ፤ የዲፕሎማሲ፤ የጦር ኃይል ወዘተ “አቅም የላትም” የሚለው ነው።

ማንም የበለጸገ አገር አቅም ኑሮት አልጀመረም። የተፈጥሮ ኀብት የሚረዳው አቅም የሌለው ኢኮኖሚ አቅም እንዲኖረው ለማድረግ ነው። ደርግ አንዷት አውሮፕላን ለወባና ሌሎች ተባዮች መከላከያ ሲሰራ አቅም አልነበረውም፡፡ ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ነበሩት። የጣና በለስን ሲሰራ እንደዛሬው የውጭ ምንዛሬ እንደልብ አያገኝም ነበር። ሌሎች ብዙ ምሳሌዎች ለመስጠት ይቻላል። የገልፍ አገሮችና ሳውዲ አረቢያ ከባዶ የበረሃ ሜዳ ተነስተው፤ የውጭ ኢንቨስተሮችን እየጋበዙ ለምተዋል። ስለሆነም፤ አቅምን ለማጠንከር አቅም አጎልማሽ የሆኑ እድሎችን ሁሉ ወደምርት ኃይሎች መለወጥ አስፈላጊ ነው። ዋናው ቁም ነገር ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው አገር ወለድ፤ በኢትዮጵያውያን ባለቤትነት የተያዘ የእድገት መሰረት መሰላሎችን ከመዘርጋቱ ላይ ነው። የተማረ የሰው ኃይል ለምርት ኃይሎችና ሌላ አቅም ግንባታ ቁልፍ ነው። የተማረው የሰው ኃይል ከተሰደደ፤ በአገር ቤት ያለው ከባከነ አቅም አይገነባም። ዛሬ ኢትዮጵያ የራሷና የሰው ኃይል እያባከነች የውጭ ልሂቃን ትሸምታለች። ህወሓት የፓርቲና የደጋፊዎች የበላይነትን ስሌት ያነገበ ድርጇት ስለሆነ የአግሪቱን የማምረት ኃይል ገድቦታል። የምርት ኃይሎችን ለማሳደግ ሁሉን-አቅፍ የሆነ፤ ፍትሃዊና ዲሞክራሳዊ አገዛዝ ወሳኝ ነው። ስለዚህ፤ የዓባይን ባለቤትነትና የተሃድሶን ግድብ ከአገዛዙ ለይቶ ማየት አከራካሪ ነው እላለሁ። አገሪቱ እርጋታ ከሌላት፤ “ከተበታተነች፤ የእርስ በረስ ግጭት” ከተከሰቱ የተሃድሶ ግድብ ዋጋ አይኖረውም።

የኢትዮጵያ መንግሥት መሪዎች ካለፈው ለመማር አልቻሉም። ጣልያኖች፤ ቱርኮች፤ እንግሊዞች፤ ግብፆችና ሌሎች ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር የፈለጉበት ዋና ምክንያት የተፈጥሮ ኃብቷንና አቀማመጧን ለመቆጣጠር ስለተመኙ ነው። ጣሊያን ወገኖቻችን በመርዝ ጋዝ

የጨፈጨፈበት ምክንያት “ኢትዮጵያውያንን ለማሰልጠን አይደለም።” ጣሊያኖች ኤርትራን የቅኝ ግዛት አድርገው በገዙበት ዘመን ህብረተሰቡን ራሱን ችሎ፤ አቅሙ ጠንክሮ፤ ተከብሮ እንዲኖር አላደረጉም። ሌላው ቀርቶ ጣሊያኖች በሚመገቡበት፤ እነሱ በሚተኙበት ወዘተ “ጥቁሮች” ተከልክለው ነበር። አስኳሉ፤ ጣሊያን ለምን ኢትዮጵያን ፈለጋት የሚለው ነው። ኢትዮጵያን በዘመናዊ መሳሪያ ለማጥቃት ሞክሮ ያልተሳካለት የምትበላ አገር ስላገኘ ነው። አንድ አስተዋይ የሆኑ ወዳጇ እንዳሉት ዛሬ ዓረቦች የሚስማሙበት ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር የተመኙትና ዛሬ ወደ ማግኘቱ የተጠጉት **<u>“የበሰለች ብርቱካን ናት”፤</u>** እንደተመኘናት አገኘናት በሚል ዘዴ ነው። እንደተባለው አንድ ጥይት ሳይተኩሱ፤ በህወሓት ጋባዢነትና አመቻችነት በልዩ ልዩ ዘዴ ባለፉት ሃያ ሶስት ዓመታት ገብተው አውታር የሆኑ የኢኮኖሚ፤ የባህል፤ የኃይማኖትና የተፈጥሮ ሃብት ምሰሶዎች ይዘዋል። ሁለመናችን አውቀዋል። ኢትዮጵያን ለማመስ እድል የሰጣቸው ህወሓት ነው። የሳውዲው ንጉስ “ሃበሻን በማባበል” የምንፈልገውን ለማድረግ እንችላለን ሲል አልተሳሳተም። ይኼም ሁኖ፤ ሳውዲ አረቢያ የኢትዮጵያን የቀን ሰራተኞች መብት ገፋ አንድ መቶ ስድሳ ሺህ ኢትዮጵያውያንን ወደ አገራቸው አባራለች። የኢትዮጵያ መንግሥት ለመብታቸው ጨኸት አላሰማም። የተፈጥሮ ኃብት መቸርቸር የማባበያ መንገድአና የበቅሺሺ ገንዘብ ማካበቻ ሆኗል። አገር ወዳድነት ዋጋ የለውም ማለት ነው። የሳውዲ መንግሥት የተመኘውን ይዞ (ለምሳሌ ለም መሬትና ወንዝ፤ የወርቅ ማእደን፤) የዓባይ ግድብ እንዳይሰራ፤ ከተሰራ እንዲፈርስ ምኞቱን የግብፅ አጋር በመሆን በይፋ ገልጿል። ዓረቦች የአገር ውስጥ ደጋፊዎች እንዳሏቸው ይነገራል። ከሌሉም እንደሚፈጥሩ የግብፅ ባለሥልጣናት ተናግረዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳየው የስርዓቱን ድክመትና ቀፎነት ብቻ ሳይሆን የእኛንም የመከፋፈል ሁኔታ ነው። እንደ ቻይና አገር ወዳድ የሆነ ስርዓትና አመራር የሌለውና በብሄር፤ ብሄረሰብ፤ ኃይማኖት ወዘተ የተከፋፈለ ሕብረተሰብ ሁል ጊዜ ለውጭ ጠላቶች ዋና መግቢያዎችን ወይንም ወንፊቶችን ይፈጥራል። ዛሬ የግብፅ ቅጥር ሰላዮች በኢትጵያ ተሰማርተው ማስረጃ ቢሰበስቡ አያስደንቀኝም።

**አገር ወዳድ የሌለበት ዓመራር አደጋ ይጋብዛል**

የግብፅን የፖለቲካ አመራርና የመንግሥት አመሰራረት ሂደት ስናይ አንድ ነገር ተከታታይነት ያሳያል። ከአሁኑ ከእኛ ሁኔታ የተለየ ማለቴ ነው። **<u>ከ 1952 የወታደራዊ አብዮት ለውጥ</u>** ወዲህ ግብፅን በበላይነት የገዙት አብዛኛውን የግብፅ ኢኮኖሚ የሚቆጣጠሩት የመከላከያ አባላት ናቸው። ዓለም ያደነቀው የታህሪር አደባባይ ሰላማዊ ሰልፍና የተከተለው የዲሞክራሲ ለውጥ ባዶ ሆኗል። በምትኩ ናስርን የሚመስል ጀኔራል የወታደር ልብሱን አውልቆ በአገር ወዳድነት፤ የግብፅን ጥቅም ለማስከበር ለፕሬዝደንትነት ተወዳዳሪ ሆኖ በዝቅተኛ ድምፅ (37 በመቶ በሚሆን) ተመርጧል። ጀኔራል አብደል ፋታህ አል-ሲሲ በጦር ኃይሎችን የእሥልምና አክራሪነትን በሚጠሉ ግብጻውያን ተወዳጅነት **<u>ያለው፤ የደህነነት ስራን በቅርብ</u>** የሚያውቅ፤ ሞርሲን ከስልጣን ያወረደ፤ ስለ ዓባይ የግብፅ የበላይነት ጉዳይ ተቆርቋሪ፤ የአምስት ሚሊዮን የመንግሥት ሰራተኞች ታማኝነት ያለው፤ አሜሪካኖች ሲያስቸግሩት ፊቱን ልክ ናስር እንዳደረገው ወደ ራሽያ ያዞረ፤ የአረብ መንግሥታት ብዙ ቢልዮን ዶላር እርዳታ በነጻ የሰጡት መሪ ነው። እንደሚታወሰው፤ ሞርሲ በኢትዮጵያ ላይ የጦር ዛቻ አሰምቶ ነበር፤ “እስከ መጨረሻ ደማችን” የሚል። በቅርቡ፤ ጀኔራሉ የዓባይን ጉዳይ በመደራደር ይፈታል ብሎ ተናግሯል። ዋናው ቁም ነገር ይህ የመሬዎችና  የግብጾች አገር ወዳድነት ኢትዮጵያን በቀጥታ እንደሚመለከት ማሰብ፤ አስቦ ሕብረተሰቡን ማገናኘት፤ ፍትሃዊ አገዛዝ እንዴመሰረት ከአሁኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የአገር ወዳድ መሪነት መስፈርት ነው እላለሁ። ግብፆች ለራሳቸው ህልውናና ጥቅም እንደሚቆሙ አልጠራጠርም።

በበላይነት ኢትዮጵያን የሚገዛው ህወሓት የዚህ አይነት የአገር ፍቅር ወዳድነት ፍልስፍና ሆነ አገዛዝ መንገድ ተጻራሪ ነው። ሆነ ብሎ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን መንግሥት በማስረከብ ወዳጅነትን ያካበተ ቡድን፤ የኢትዮጵያን የባህር በር የዘጋ፤ ሕዝብን ከሕዝብ ያናከሰ፤ ታሪክን የከለሰ ወዘተ መንግሥት ለተከታታይ ትውልድ አብሮ መኖርና አብሮ ማደግ ደንታ የለውም። ኢትዮጵያን ከአደጋ ለመታደግ፤ ሕዝቧን ከፍፁም ምስኪንነትና ከጥገኝነት፤ ወጣቱን ከስደት፤ ሕዝቡን ከእርስ በርስ “እልቂት” ለማዳን ፍላጎት ያለው አይመስልም። ቢኖረው አሁን የሚያደርገውን አሰቃቂ ግድያና አፈና ያቆም ነበር። ዛሬም እንደትላንቱ ተገዢነቱ ለስልጣንና ሃብት ለማካበት መሆኑ በግልፅ ይታያል። የግብፅ ባለስልጣናት ይኼን የህወሓትን ድክመትና ስግብግብነት በሚገባ ያውቃሉ።  የህወሓት መንግሥት በድንገት ቢፈራርስ ዋናው ተጠቃሚ ግብፅ ይሆናል ማለት ነው። በጥላቻ አንመራ፤ ጥላቻን አናስፋፋ፤ አናባብስ፤ የጥላቻ ፖለቲካ መጋቢ አንሁን የምለው ለዚህ ነው። የሚያዋጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ላይ፤ ለአንድ አገር፤ ለፍትህ-ርትእ፤ ለእውነተኛ እኩልነትና ዲሞካራሲ ይነሳ የሚል መርህ ብቻ ይመሰለኛል። የማንክደው አስኳል ጉዳይ፤ ከጦር ኃይላቸው የበለጠ፤ ግብጾች በዓባይ ዙሪያ ብሄራዊ አንድነት አላቸው። በቁጥር ሶሥት ያቀረብኩት መሰረታዊ ሃሳብ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊያሳስብ የሚገባው ዋና ነገር የግብጾች የጦር ኃይል አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በብሄር፤ ብሄረሰብ፤ ጥቅምና ኃይማኖት መበታተኑ ነው። መፍትሄው የማንም ሳይሆን የራሳችን ነው።

**ፍትሃዊ ያልሆኑ ስርአቶች አደጋ ፈጣሪ ናቸው**

ታሪካችን ድክመቶች እንደነበሩት አያከራክርም። ማንኛውም አገር በድክመትና በአብዛኛው በእርስ በርስ ጦርነት ያለፈ መሆኑን አሳይቻለሁ። እኛ ይኼን የታሪክ ሂደት አለመቀበላችን የድክመታችን መስፈርት ሆኗል። ፍትሃዊና አሳታፊ የሆነ የመንግሥት ስርዓት ቢኖር ኑሮ ለውጭና ለውስጥ ተጻራሪዎች ወንፊት አንሆንም ነበር። በተፃራሪው፤ ፀረ-ፍትህ፤ ፀረ-እኩልነት፤ ፀረ-ዲሞክራሲ የሆነ ስርዓት ለጊዜው ጠንካራ ቢመስልም ግጭት ፈጣሪ መሆኑን በልዩ ልዩ አገሮችና በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ አይተናል፤ እያየን ነው። ከላይ ባጭሩ እንዳሳየሁት፤ ኢትዮጵያ ሁል ጊዜ የውጭ ኃይሎች አይናቸውንና ኃይላቸውን ያዘወተሩባት አገር ናት። ፍትሃዊ ስርዓት፤ ሁሉን

አሳታፊ የሆነ ኢኮኖሚ ካልተመሰረተ ሁኔታው ይቀጥላል። አድልዎ፤ የተዛባ ገቢ፤ ጥሪትና ልማት ግጭት ፈጣሪ ነው። የውጭ ኃይሎች ፍላጎት በባዶ ነገር ላይ የተቀነባበረ አይደለም። በተፈጥሮ አቀማመጥና ሃብት ላይ ያተኮረ ነው። የኢትዮጵያ የአስተዳደር፤ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ኋላ ቀርነቷ የችግር መጋቢዎች ነበሩ ለማለት የሚያስችሉ ብዙ ምሳሌዎች አሉ። ከነበረው ሁኔታ አንጻር ሲታይ ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት ለኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነት፤ ኢትዮጵያዊነትና ስልጣኔ ትኩረት ለመስጠት መሞከራቸው አይካድም። በዘመናዊነትና ሁሉን የማህበረሰብ ክፍሎች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በማስተናገድ መስፈርቶች ሲታይ ተከታታይ መንግሥታት ኋላ ቀር ናቸው የሚለውም አያከራክርም፡፡ በጥንካሬ መስፈርት ሲታይ፤ በቅድመ ህወሓት ስልጣን የነበራቸው መንግሥታትን ከአሁኑ ስርዓት የሚለያቸው አንዱ ባህርይ በስልጣን ውሳኔና የሰው ኃይል ስርጭት ተሳትፎ የአገሪቱን ስብጥር ሕዝብ  እንዲያንፀባርቅ ጥረት ማድረጋቸው ነው። ይህ በስብጥርነት ማመን ጥንካሬ ነው። የመከላከያ ኃይሉ አወቃቀር ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። ይህ የተደረገበት ዋና ምክንያት ስብጥር የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን እምቅ የተፈጥሮ ፀጋ ጥቅም (inherent natural potential) በማጤን ነው። ድክመቶች ያሏቸው መሆኑ እንዳለ ሆኖ እነዚህ አገር ወዳድ መሪዎች የአገሪቱን ብሄራዊ አንድነትና ነጻነት ለመታደግ ያደረጉት ጥረት ሊካድ የሚችል አይመስለኝም። ያለፈውን ስርዓት ሁሉ ህወሓት በፈጠረብን የጥላቻ አይን ካየነው ግን ምንም ጠቃሚ ስራ አለተሰራም ከሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን። ህወሓት/ኢህአዴግ ሲለወጥም ተመሳሳይ ትችት ማቅረባችን አይቀርም። አንዳዶቻችን ነገሮችን በማወላገድ የተካንን እንመስላለን፤ በማንኛውም ነገር ጥሩ ክስተት አናይም። የኢህአዴግ መንግሥት ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ ብዙ መሰረተ ልማቶች ሰርቷል የሚል ሃሳብ በመሰንዘሬ አንዳንድ አንባቢዎች ቢሰራም ለምን "ይኬን አልክ" ያሉ አሉ። መንግሥቱ ኃይለማሪያም ከማንም የበለጠ የራሱን ቤተሰብና ህይወት ገለል አድርጎ ሰርቶ ነበር ስላልኩ እንዴት ይኼን ትላለህ ያሉ አሉ፤ ወዘተ። ታዲያ እውነቱን ከውሸቱ ለመለየት ካልቻልን መማራችን ምን ትርጉም አለው? ባጭሩ፤ በተለያዩ ወቅቶች የኃይለ ሥላሴንና የደርግን መንግሥታትም እንደዚሁ በይነንባቸው ነበር። ሃቅን በማስረጃ ደግፎ ማቅረብ ሃጢአት የሆነበት ሕብረተሰብ እየፈጠርን መሆኑን ያሳያል። አሁን ያለው ሃቅ የሚታይ፤ የሚዳሰስ ነው፤ መሰረተ ልማት ተሰፋፍቷል። የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ አልተሻሻለም። የተከታታይ አምባገነናዊ መንግሥታ፤ ህወሓት/ኢህአዴግን ጨምሮ፤ ደካማ ጎናቸው የመላውን ሕብረተሰብ ፍላጎትና መብት አለማወቃቸው፤ ለፍትህ-ርትእ፤ ለሕዝብ **<u>ስልጣን፤ ለእውነተኛ እኩልነት፤</u>** ለመዋቅራዊ ለውጥ ወዘተ ቆራጥና ደፋር በሆነ ደረጃ አለመመስረታቸው፤ አንዲያውም ለእነዚህ ለውጦች ማነቆ መሆናቸው ነው። ቁም ነገሩ፤ እድገትንና ልማትን በጭፍን ጥላቻ አንየው ማለቴ ነው። ጥንካሪዎችን ሳንክድ፤ ድክመቶችን በማስረጃ ለማቅረብ እንችላለን።

ለምሳሌ፤ የአጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት ለኔ ትውልድ የትምሕርት እድል ከፍቷል። የአፄ ምኒልክ መንግሥት ዘመናዊ መገናኛ መስርቷል ወዘተ። ሊካድ አይችልም። ህወሓትና መሰሎቹ እንድንቀበል ያስገደዱንና ተከታታይ ትውልድ እንዳያውቀው የሚጥሩት ያለቱፍ መንግሥታት ትተውልን የሄዱት መልካም ቅርስ (Legacy) የለም የሚል ነው። ልክ ኢትዮጵያ ትላንት የተመሰረተች ናት ለማለት። አገሪቱን ከጨለማ ዘመን ነጻ ያወጣናት እኛ ብቻ ነን ለማለት። እርግጥ ነው፤ በተጻራሪው የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በሃገሪቱ የተከሰቱትን ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ችግሮች በጥሞና አመዛዝኖ ጃፓን፤ ታይላንድ ወይንም ሌላ ረጅም ታሪክና የበለፀገ ባህል ያላቸው ዘመናዊ አገሮች ያደረጓቸውን ለውጦች አላደረገም። በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ራስን ለመለወጥ አለመቻልና አለመፍቀድ፤ ለሕዝብ ብሶት ዋጋ አለመስጠት ያስከተለውን እልቂት በእኛ ትውልድ አይተናል። ችግሩ እኛም ከነሱ ተሸለን አለመገኘታችን ነው። አሁንም ያለፈውን እየደገምነው ነው። የዛሬው ዘመናዊነት ፎቅ፤ መንገድ፤ ግድብ፤ የትምኅርት ተቋሞች ወዘተ ላይ አያቆምም። ዋናው የዘመናዊንት መስፈርት የሕዝብን ኑሮ ከማሻሻሉ፤ የሕዝብን ክብርና መብቶች በሕግ ከማስከበሩ፤ ብሄራዊ ትሥስር ከመመስረቱ፤ መንፈሳዊነትን ከማጠናከሩ፤ ከሌላው ጋር አብሮ የመኖርና የማደግ ፍላጎቱን ከማጎልመሱ፤ ለወጣቱና ለተከታታይ ትውልድ ልዩ ትኩረት ከመስጠቱ ወዘተ ላይ ነው። ቻይና ይኼን ታደርጋለች፤ ህወሓት ተጻራሪውን ያደርጋል። በተናጠል የተሃድሶ ግድብ መብትንና የግለሰቦችን አቅም ግንባታ ክብርና ማንነት አይተካም። እኔ እድገትንና ልማትን ለማየት የምሞክረው ከእንዚህና ከሌሎች የተያያዙ መሰረታዊ ለውጦች ጋር በማያያዝ ነው።

**የአገዛዝ ስህተቶችንና ባህሎች መደጋገም ለማንም አይበጂም**

ዛሬ ካለፈው ድክመትና ችግር ያልተማረው ህወሓት ለሕብረተሱ ምስቅልቅልነትና አቅጣጫ ማጣት ዋና ምሳሌ ነው። አንዳንዶች የህወሓት አመራር የማይለወጠው ራሱ በፈጠረው የፍርሃት ባህል አዙሪኝ ውስጥ ስለገባ ነው ይላሉ። ሊሆን ይችላል። ፍርሃት ካለ ማንን ተቃዋሚ አነጋገረና መፍትሄ ፈለገ ብለን መጠየቅ ተገቢ ነው። የሚነጋገረውና የሚመካከረው ከራሱ ባልደረቦች ጋር ብቻ ነው። ዘጠና አራት ሚሊዮን ሕዝብ እየገዙ ዝግ ችሎት ማካሄድ ዘመናዊነትና ብልሃተኛነት አይደለም። "በትግል ያገኘነውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅምና የበላይነት አናጣለን፤ የመጣውን አመፅና አደጋ ሁሉ በሃይል መወጣት አለብን" የሚል ከፍርሃት ጋር የተያያዘ "ስልጣን ወይም ሞት" መርህ ጊዜ ያለፈበት ፍልስፍና ነው። በውይይትና በድርድር ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን ማነቆ ማድረግ አደጋውን ያባብሳል እንጂ አይፈታም። **<u>ብልሃት (Wisdom) ያለው ዓመራር ችግሮች እንዲፈቱ አግባብ ያላቸውን የፖለቲካ፤ የኃይማኖትና የማህበረሰብ ስብስቦችንና ታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ ለውይይት ጠርቶ ለእርቅና ለሰላም ማነጋገር አስፈላጊ ነው እላለሁ።</u>** ጋዜጠኞችን እያሰሩ፤ የኦሮሞ ተማሪዎችን እየገደሉ፤ አማራውን እየገደሉና ከመሬቱ እያፈናቀሉ፤ የጋምቤላን መሬት እየሸጡ ወዘተ ሰላምና እርጋታ እንፈልጋለን ማለት በሕዝብ ላይ መቀለድ ነው። የህወሓት ግትርነት ለራሱም አደገኛ መሆኑን አውቆ ሁሉን አስተናጋጅ ለሆነ አማራጭ ቆርጦ መነሳት የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። አገሪቱን በብሄር ወይንም በኃይማኖት፤ ወይንም በጥቅም ለያይቶ ማጥቃት ለሃያ ሶስት ዓመታት ማገልገሉ ባይካድም ዘላቂነት የለውም። ስርዓቱ ያገለለው የሕብረተሰብ አካል ዘጠና በመቶ የሚሆነውን ነው። ጥቂቶች "ቃተኛ" ስለበሉ አብዛኛው ሕዝብ በልቶ አደረ ማለት አይደለም። ድህነት የሚታይ፤ የሚዳሰስ ክስተት ነው። ወጣቱ ትውልድ ለራሱ

እድል ሲል መታገሉ የማይቀር ነው። “ስደት በቃኝ፤ መታፈን በቃኝ” ብሎ በመነሳት ላይ ይገኛል። ህወሓት ወጣቱ ትውልድ በፍርሃት ዓለም እንዲኖር ማስገደዱ ብቻ ሳይሆን በኑሮውም ወደ መጥፎ ልምዶች እንዲሸጋገር ያደረገው ጥረት ቀስ በቀስ የውሃ ሽታ እየሆነ ነው። ወጣቱ ትውልድ ታሪኩን እንዳያውቅ፤ በራሱ እንዳይተማመን የተደረገው አጥፊ ሂደት ቀስ በቀስ በእምቢተኛነት እየተተካ ነው። ህወሓት ከኢትዮጵያና ከስብጥር ሕዝቧ አኩሪ የመቻቻል ባህል ለመቅሰም ያልቻለውን ወጣቱ ትውልድ በሚያደርገው ሰላማዊ ሰልፍ እያሳየ ነው። **ወጣቱ ትውልድ “ ኢትዮጵያ ሃገሬ ናት፤ ዜግነቴ ኢትዮጵያዊ ነው” ማለት ጀምሯል።** ልክ ቻይኒሶች፤ ህንዶች፤ ችሊያኖች፤ ብራዚሊያኖች ወዘተ የሚሉት ማለት ነው። ወደ ብሄራዊ ማእከል መንቀሳቀስ ተጀምሯል ማለት ነው። ይህ ሂደት ተስፋ የሚሰጥ ነው። ሌሎችችን መደገፍ አለብን እላለሁ።

የህወሓት መሪዎች የተከተሉትና አሁንም የሚከተሉት የሃሳብ፤ የሰነ ልቦና፤ የፖሊሲ፤ የእድገትና የጥቂቶች የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ባህል የመነጨው በኢትዮጵያውያን ውይይት፤ መመካከርና ድጋፍ አይደለም። ከላይ የተጫነ ሸክም ነው። ህወሓት የፈጠረው ችግር ይገባናል የሚለው ክፍል ብዙ ነው። ችግሩ ከገባን ለምን በአንድ ላይ ለመነሳት አልቻልንም? ተመራምሬ ለማግኘት ያልቻልኩት ብሄራዊ የሆነ የማህበረሰብ ስብስብ እና እርዮት (A Sense of National Cohesion and Synergy and Vision ) አለመኖሩን ነው። ችግሩ ህወሓት ብቻ አይደለም ማለት ነው። እኛም ነን። ህወሓት የሚከተለው የእድገትና ዘመናዊነት ፍልስፍና ከውጭ የተሸመተ የኪራይ ሰብሳቢነት ስልት ነው የሚሉ ብዙ ናቸው። ሆኖም አማራጩ ምንድን ነው ለሚለው መለስ አልተሰጠም። ግንቡና ቤቱ የዘመናዊነት፤ የልማትና የማንነት መለያ አይሆንም፤ ድህነት ተባብሷል፤ አፈና ብሷል የሚሉ ብዙ ናቸው። አማራጩ ምንድን ነው ለሚለው መለስ አልተሰጠም። ህወሓት ከመንደር ጀምሮ በመከፋፈል በጥላቻ መረብ የተዘረጋ ስልት ከቅኝ ገዢዎች፤ ከጣሊያኖችና ከእንግሊዞች፤ ከአረቦች፤ በተለይ ከግብጾች የተሸመተ ይመስላል የሚሉ ብዙ ናቸው። ሆኖም አርዓያ ለመሆን እርስ በርስ ያለውን መጠላለፍ፤ ለዝናና ለመታወቅ፤ ለጥቅምና ለስልጣን የሚደረግ እሽቅድምድም ለማቆም የሚሞክሩ ጥቂቶች ናቸው። ክፍፍሉ ለአጥቂዎች አመቻቸ ነው የሚሉ ብዙ ናቸው። ሆኖም፤ ከህወሓት ላይ ከመጮህ ባሻገር የተለያዩ የብሄር፤ ብሄረሰብ ተቃዋሚ ክፍሎች አሁንም ሆድና ጀርባ ሆነው ይሰራሉ። **ባለፉት ሃያ ሶስት ዓመታት፤ በተለይ ቅንጅት ከፈራረሰ በኋላ የአማራው፤ የጉራጌው፤ የአፋሩ፤ የወላይታው፤ የኦጋዴኑ፤ የትግራዩ፤ የኦሮሞው፤ የአኟኩ ወዘተ ምሁር፤ልሂቃንና የፖለቲካ ስብስብ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ሆኖ ለሃገሩና ለወገኑ የተወያየበት ቀን አይገኝም።** ይኼን ለማድረግ የህወሓት ፈቃድ አያስፈልግም፤ ፈቃደኞች ከሆን ለማድረግ እንችላለን፤ መደረግም አለበት።

መከፋፈላችን፤ ሆድና ጀርባ መሆናችን የሚጠቅመው ለገዢው ፓርቲ የስልጣንና የኢኮኖሚ ጥቅም ቆይታ ነው። በተጨማሪ፤ ይህ የተቃዋሚው ክፍል ሆድና ጀርባ መሆን ለውጭ ኃይሎች በጦርነት የማያገኙት ክፍተት ፈጥሮላቸዋል። ተቃዋሚው ክፍል ራሱን ካልለወጠ ስርዓቱን ለመለወጥ አይችልም።

ያለፈው የፖለቲካ ታሪካችን በተደጋጋሚ ያሳየን የውስጥ ክፍፍል ለውጭ ኃይሎች መጋቢ ጭምር መሆኑን ነው። በቁጥር አንድ እንዳሳየሁት፤ በአፄ ኃይለ ሥላሴና በደርግ ዘመን የኢራኩ ሳዳም ሁሴን፤ የሶሪያው አሳድ፤ በተለይ፤ የግብፅ ተከታታይ መሪዎች ከፈርኦኖች ጊዜ ጀምሮ የተከተሉት ፍልስፍና የተያያዘና ተከታታይነት ያለው ነው። ኢትዮጵያ ከአውሮፓና ከዓረብ አገሮችና ጋር ለመወዳደር አትችልም፤ መወዳደር የለባትም የሚል። ሕብረተሰቧ በብሄር ብቻ ሳይሆን በጎጥና በኃይማኖት መከፋፈል፤ ኢኮኖሚዋ ጥገኛ ወዘተ መሆን አለበት የሚል። የአድዋ ብሄራዊ ድል ይኼን አስተሳሰብ ቢለውጠውም አገሪቱ ሰላምና እርጋታ አግኝታ አታውቅም። ለምሳሌ፤ ደርግ የወደቀበት ዋና ምክንያት ለሃገሪቱ ጥቅም ስላልቆመ አይደለም። በውስጡ ያለውን ቅራኔ በብልሃት አለመምራቱም ብቻ አይደለም። ደርግ በውስጡ ብዙ ራሳቸውን አገልጋዮች፤ የውጭ መንግሥታት ተወካዮች፤ “ከሃዲዎችንና” ስላዮች ስለነበሩብት ጭምር ነው። በዚህ ዙሪያ ብዙ የተፃፉ ማስረጃዎች አሉ፤ ወደፊትም የሚወጡ እንዳሉ እገምታለሁ። ለደርግ መውደቅ ምክንያት ከሆኑት መካከል በማስረጃ የደረስኩባቸውንና እኔ የማውቃቸን ብቻ ልጥቀስ።

አንድ፤ የሶማሌ ወረራ፤

ሁለት፤ የእርስ በርስ ጦርነት፤

ሶስት፤ የአሜሪካኖች ተጽእኖ፤

አራት፤ የአረቦች ተወካይ ታጋዮች ማጎልመስ፤

አምስት፤ የአገር ውስጥ ጥቅም ፈላጊዎች፤ ወዘተ ይገኙበታል።

ከሁሉም በላይ ግን ኢትዮጵያን ያደከማትና የጎዳት የውስጥ መከፋፈልና መተላለቅ ነው። ቁም ነገሩ ያለፈውን ለመመርመር ወይንም ለመተቸት አይደለም። ህወሓትን ወደጎን ትተን ተቃዋሚ ነን የሚሉ ክፍሎችን ስናይ፤ አሁንም በተመሳሳይ ደረጃ የክፍፍሉን አደጋ አላጤኑትም ለማለት ነው። በውስጣቸው ሰላዮች፤ ጥቅም ፈላጊዎች፤ አዲስ ተወዳጆች ወዘተ ተሰማርተዋል። ተቃዋሚው ክፍል የራሱን ድርጂት ለማጽዳትና ለመከላከል አልቻለም። ትኩረቱ ህወሓትን ከመቃወሙ ላይ ብቻ ስለሆነ የዓለም ሕብረተሰብ ተቃዋሚው ክፍል ለምን ዓላማ፤ ለምን ራእይ እንደቆመ አያውቅም። ለምን እንደተከፋፈለ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ቀርበው መልስ አላገኙም። መቃወምና ብሩህ የሆነ አማራጭ ማቅረብ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የኔ ትውልድ የአፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ይቃወም ነበር። ሆኖም፤ ለመተካት የሚፈልገውን አዲስ ስርዓት፤ ማለትም ሶሻሊዝምን በሚገባ አጥንቶና ተንትኖ ወደ ስራ ለመተርጎም የተዘጋጀ እንደነበር

አይካድም። የግራው ክንፍ በአንድ ላይ አልቆመም ተብሎ ይከሰስ እንደሆን እንጂ አቅጣጫ የለውም ለማለት ማስረጃ የለም። ራእይ ነበረው። አገሪቱን ወደ የት ለመምራት እንደፈለገ ያውቅ ነበር። ነበር ሆኖ ቀረ እንጂ።

***ምን ይደረግ?***

በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያውያን በጎሳ ተለያይተው ሕዝቡን ወደ ከፋ እልቂት ቢያሽጋግሩት ተጠያቂዎቹ ሁላችንም ነን። ምን አደረግን፤ ምን ሰራን፤ መማራችን ከየት ላይ ነው? ካለፈ ተምረን ስናየው ገዢውም ፓርቲ ሆነ ተቃዋሚው መገንዘብ ያለበት፤ ለወደፊቱ ትውልድ ራእይ የሌለው፤ ሰላምና እርጋታን ፍሬቢስ አድርጎ የሚያይ የፖለቲካ ስብስብ ለሃገር ሆነ ለማህበረሰብ ፍትህ፤ ዘላቂና ፍትሃዊ እድገት ማሰቡ አከራካሪ ነው። የምናውቀው አንዱና ዋናው ተከታታይ ማነቆ ኢትዮጵያ ለሁሉም ፍትሃዊ የሆነ የመንግሥት ዓመራር ፈጥራ በተፈለገው ፍጥነት ለማደግና ጥቅሟን ለማስከበር አለመቻሏ ነው። ላለመፍጠሯ ተጠያቂዎች ያለፉት አይደሉም፤ ህወሓትም አይደለም። ሁላችንም ነን። ለምሳሌ፤ ደርግ አገሪቱን በሁሉም ዘርፍ ለማስቀደም ሞክሮ ነበር። የተማረው ክፍል (Modernizing Elites) በተለይ የሶሻሊስት እርዮት ተከታይ የነበረው የፖለቲካ ስልጣን እሽቅድምድምን ከአገርና ከህዝብ ጥቅም በላይ ማድረጉ አገሪቱን ጎድቷታል። ማስረጃው ህወሓት ባቋራጭ የፖለቲካ ስልጣን መያዙ ነው። የማይካደው በደርግ መንግሥት የነበረው የእርስ በርስ እልቂት፤ **<u>ለውስጥና ለውጭ ተቀናቃዮች ወንፊት ሆኗል።</u>** የተማረው ኃይል እርስ በርሱ ስለተጋጨ የደርግ መንግሥት ወታደራዊ የበላይነት ይዞ የዲሞክራሲውን አብዮት ወደ ፍጹም አምባገነናዊ መንግሥት ለውጦ የእርስ በርስ ጦርነት እንዲስፋፋ ምክንያቶ ሆኗል። የኔ ትውልድ የነበረውን የእውቀትና የፖለቲካ ብስለት ማነስ፤ የኃይሎችን አሰላለፍ፤ የውጭ አገሮችን ሴራ፤ የጎሰኛነት ፖለቲካ ግስጋሴና አደጋ፤ የመወያየትንና የመቻቻልን ጥቅም፤ የሃሳብ ልዩነቶችን ከግለሰቡ የመለየት ጥቅም፤ የወደፊቱን ያልታሰበ አደጋ የመመራመርና ለአደጋው የተለያዩ አማራጮችን የማቅረብ ብልሃት ወዘተ ለማስተናገድ አልቻልነም ነበር። ብንችል ኖሮ ዛሬ ወደገባንበት የፖለቲካ አዙሪኝ አንገባብ ነበር የሚል ብምት አለኝ። የጥበበኞች አለሞኖር፤ ቢኖሩም መታፈን፤ አዳማጭ ማጣት፤ ወይንም ከፖለቲካው ዓለም መወገድ ኢትዮጵያን ጎዳት። ብዙ ጊዜ የማይነገረውና የማይካደው በደርግ ውስጥም ሆነ ከደርግ ውጭ አገር ወዳዶች ነበሩ። ብዙ አገር ወዳድ ምሁራን ነበሩ። ከራሳቸው ጥቅም በላይ አገሪቱንና ሕዝቡን ያስቀደሙ የግራ ክንፍ አባላት ነበሩ። በአብዛኛው አገር ወዳድ የሆነው ክንፍ አገሪቱ ብቁነት ያላቸው፤ ከሁሉም ብሄር፤ ብሄረሰቦች የተሰባሰቡ ዜጉቿ እንዲታቀፉና እንዲሳተፉ ከፍተኛ አስትዋፆ አድርጓል። አሁንም በኢህአዴግ ውስጥ አገር ወዳዶች የሉም ለማለት እንደማንችል አሳስባለሁ። ድምጻቸው ስላልተሰማ የሉም ለማለት አንደፍርም። ለማሳሰብ የፈለግሁት ካለፈው ስህተት ተምረን መደጋገሙን እናቁም ነው። እልቂት ከተጀመረ ውርደቱ ለሁላችንም እንደሚሆን አንጠራጠር።

በደርግ ጊዜ ያየሁት ክስተት ነበር፤ አሁንም የሚካሄድ። የተማረው ክፍል እርስ በርሱ ለመተማመን አልቻለም ነበር።

ልክ በመለስ ዘመን እንዳየነው ሃቁን ለመናገር አንደበት የነበረው ክፍል የተወሰነ ነበር። ሁሉም ለከፍተኛው ባለስልጣን "እሺ" ባይ ሲሆን ልዩ ልዩ አማራጮችን ለማየት አልተቻለም። እውነቱ ውሸት ይሆናል። ገንዘብና ግንኙነት ያለው በክፉ ቀን ቤተሰቡንና ንብረቱን ከሃገር ሲያሸሺ (ዛሬም እየሆነ ነው) በወቅቱ የሚታመንና የሚደጋገፍ ሰው መኮብለሉና አለመገኘቱ ለአገሪቱ ትልቅ በደል ፈጥሯል። በመንግሥት ደረጃ ሲታይ፤ በአመራሩ ውስጥ የነበረውን አሻጥር ለመገመት አያስቸግርም። ስብጥር የሆነ አመራር ያለ መተማመን ሊሰራ የማይችል መሆኑን ያሳያል። ሁሉም የሚሰራው ለብሄሩ፤ ለፓርቲው፤ ለቤተሰቡ፤ ለግል ጥቅሙ፤ ለውጭ አገር መንግሥታት ወዘተ ከሆነ ሃገሩን ተቀዳሚ አያደርግም ማለት ነው። ህወሓት ይኼን የመካካድ፤ የስግብግብነት፤ የግል ጥቅም ፈላጊነትና የፍርሃት ባህል ስላወቀ ታማኝ ለሆኑ ለትግራይ ተወላጆች ተቀዳሚ ስልጣን ይሰጣል። የህወሓት የአገዛዝ መቆያ ዘዴ ታማኞችን መሸመት፤ አጋር እንዲሆኑ ማባበል፤ በጥቅም መግዛት ነው። ስጋውን በልቶ አጥንት ጥሎለት አንተም ተጠቃሚነህ ይለዋል፤ ተቀብሎ ደጋፊ የሆነው ብዙ ነው። ፍርፋሬህን አልፈልግም የሚል ጎበዝ ጠፍቷል። ተጠቃሚ የሆነ ለጥቅሙ ሲል ስርዓቱን ይደግፋል። በደርግም ወቅት፤ ሁሉንም ይወክላል ባይባልም፤ የነበረው አሳፋሪ የራስ ወዳድነት፤ ስግብግብነት፤ ሺሙጠኛነትና ከሃዲነት ለስርዓቱ መፍረስ ከፍተኛ አስተዋፆ አድርጓል። አስቸጋሪ ሁኖ የምናየው-- የራስ ወዳድነት፤ የመደለል፤ የስግብግነት-- ባህል ችግሩ በሃገር ደረጃ ሲታይ፤ የኢትዮጵያ ተከታታይ ትውልድ ለራሱ ብቻ ሳይሆን-- ልክ ቻይናዎች እንደሚያደርጉት-- ለሃገሩም እንዲያስብ፤ ጠበቃ እንዲሆን ለሚደረገው የተቀደሰ ጥሪ በክሎታል፤ እንዲያውም አግቦታል። ወጣቱ ትውልድ ለራሱ የወደፊት ጥቅም ሲል የሃገሩንና የመላውን ሕብረተሰብ ቀን የማይሰጥ ግዴታ መቀበል አለበት። ሌሎቻችን ካለፈው ስህተቶች ተምረን በተደጋጋሚ እድሎች እንዳያመልጡን አብረን የምንሰራበት ወቅት አሁን ነው። ክሱንና ወቀሳውን እንተወው ማለቴ ነው። ኢህአፓን፤ መኤሶንን፤ እሴፓን፤ አፄ ኃይለ ሥላሴን፤ መንግስቱ ኃይለማሪያምን ከመውቀስ ባህል ወደ መቻቻል፤ ወደ ጨዋነት ወደ መከባበር፤ ወደ መፈላለግ ባህል እንሸጋገር እላለሁ። ህወሓት እርስ በርሳችን እንድንተራመስ፤ እርስ በርሳችን እንድንጋጭ፤ እርስ በርሳችን እንዳንተማመን የበከለን በቂ ነው ለማለት እንድፈር። ወጣቱ ትውልድ የሚፈልገውና የሚመኘው ብሩህ፤ ሁሉን አሳታፊ፤ ፍትሃዊና ዲሞክራሳዊ ስርዓትን እንጅ የጎሳ ጥላቻን አይደለም።

**ሌላ እድል አያምልጠን**

የዓባይንና የሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶችን የወደፊት ጥቅም ስናጤን መርሳት የሌለብን ተከታታይነት ያለው ሃቅ ኢትዮጵያ ካልጠነከረች፤ ሕዝቧ ከድህነት ነጻ ካልወጣ፤ ወጣቱ ትውልድ በሃገሩ የስራ እድል ካላገኘና ሕዝቡ ከጎሰኛነት ባሻገር በእኩልነት አብሮ ለመኖር ካልቻለ የውጭ ኃይሎችና የውስጥ ተቃዋሚዎች ጥረቶች ስኬታማ ይሆናሉ። ፍትሃዊና ዲሞክራሳዊ ስር ዓት ምኞት ብቻ ይሆናል። የዓለም ሕብረተሰብ እንደናቀን ይቆያል። በአንድ አበይት ጉዳይ ላይ እንስማማ። ኢትዮጵያን ከመፈራረስ፤ ሕዝቧን ከከፋ እልቂት ለመታደግ የሚችለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው። ሌሎቻችን ጥላቻን ከማራገብ ይልቅ የሰላምንና የእርቅን ጥቅም ብናስተምር የኢትዮጵያና

የዓለም ሕዝብ ያከብረናል። ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን ያከብሩናል። ይኼን ለማድረግ የማይገኝ እድል ከፊታችን አለ። ጥላቻን እናስወግድ የሚል እድል። ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ይካሄድ የሚል እድል። የሕዝብ መብት ይከበር የሚል እድል። አፈናና እልቂት ይቁም የሚል እድል። ዲሞራሳዊ ስርዓት ይመስረት የሚል እድል። እነዚህ ሁሉ የጋራና ሊደረጉ የሚችሉ ምኞቶች ናቸው። መተባበርን ይጠይቃሉ።

ህወሓት ፈቃደኛ ሆኖ ነገ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ቢደረግ ተቃዋሚው ክፍል እንደሚያሸንፍ ይገመታል። ሆኖም፤

አንድ፤ ለማሸነፍ መደረግ ያለበትን ቅድመ ዝግጂት በአንድ ላይ ሆነን አልሰራነም። እድሉ እንዳያመልጠን ከፈለግን አብሮ መስራት የሁላችንም ግዴታ ነው፤

ሁለት፤ ተቃዋሚው ክፍል ቢያሸንፍ ከዚያ በኋላ የሚደረገው ድርድር፤ የመንግሥት አቀራረጽና ዓመራር ምን መልክ እንደሚይዝ ምንም አይነት ውይይት ሲደረግ አይታይም። የኢትዮጵያ ልሂቃን በህወሓት መጥፎ ስራ ላይ በማተኮር ፋንታ--ችግሩን የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሚያውቀውና በየቀኑ በየቤቱ ሁኖ ስለሚተችበት--አማራጭ ሃሳቦችን የማቅረብና የመወያየት ግዴታ አለብን።

ባጠቃላይ፤ **<u>ኢትዮጵያውያን በያለንበት ከዓባይ የተሃድሶ ግድብ ባሻገር ማሰብና</u>** መወያየት አለብን። የወቅቱ አነጋጋሪ ጉዳይ የኢትዮጵያ መኖር አለመኖር እና ህወሓት የፈጠረው የጎሰኛነት ፖለቲካ የእርስ በርስ ግጭት ከቁጥጥር ውጭ አልፎ "እልቂት" (Ethnic Genocide) እንዳያስከትል መደረግ ያለባቸውን ውይይቶችና ዝግጅቶች በፅሞና ማጤንና መስራት ነው። ፈቃደኛ ከሆንን እነዚህን የተቀደሱ ዓላማዎች ለማድረግ እንደምንችል አልጠራጠርም። እውቀቱ፤ የሰው ኃይሉና ገንዘቡ አለ። የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ የአሁኑና ተከታታይ ትውልድና ታሪክ የሚጠይቁን በቀውጢው ቀን የት ነበራችሁ እንደሚሆን አንጠራጠር። እድሉን አናባክነው እላለሁ።

ክልፍ አምስት የቅድመ ህወሓት መንግሥታት ስለ ዓባይ ያደረጉትን ጥረትና የግብጾችን አቋም ያቀርባል።